**ከኪዳናዊ አክሊለ-ጊዮርጊስ የደረሰ እ-ጦማር፦**

**+ዮም ፍሥሓ ኮነ!**
**በእንተ ፍልሰታ፡ ውስተ አርያም!**
**ለእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም!+**

**ጤናውን ይስጥልኝ፣ በእግዚኣብሔር መንግሥት፣ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን እኅቶቼና ወንድሞቼ! እንደምን ኣላችሁልኝ!?**

**ቤተሰቤና እኔ፣ በቸሩ ፈጣሪ እርዳታ፣ በፍጹም መልካም ሕይወት እንገኛለን፤ ምስጋናችሁ ዛሬም ይድረሳቸውና።**

**በዚህች እ-ጦማሬ ላስተላልፍ የፈለግኍትን ኣስተያየትና የሃሳብ ጥቆማ- የኪዳናዊ ጋሽዬ ኤርሚያስ ከበደ ቃለ መጠይቅ ሥዕላዊ መጽሔትን በተመለከተ- ሥዕላዊ መጽሔቱን ስመለከት፡ ገና ከመነሻው ላይ በተመለከትኩት፣ እንደእኔ እምነት ግን ትክክለኛ ኣይደለም ብዬ በያዝኩት፣ የምንኖርባትን ዓለም ሥዕላዊ መግለጫ ወይም የቅርፅና ሕልውና ጉዳያን በተመለከተ ነው።**

**እርሱውም፣ በኣጭሩ ለመጥቀስ ያህል፣ መንፈሳውያን የኾንነውና የፈጣሪን እውነትና እምነት የምንከተል እንደማንስተው የምነው ጉዳይ፣ ፈጣሪ ከእና ሰብኣውያን ፍጥረቱ በፊት ውብና ድንቅ ኣድርጎ ሠርቶ ያቆየልን "ዓለም"፣ "ምድር" የምንላት የባህሩን ውሃና የየብሱን ኣካል የያዘችው፣ እንዲሁም በጠፈር ሰማይ ሥር ብርሃናቶቿን የምታጎናጽፈን መኖሪያ ገነታችን፣ ያላት የኣቀማመጥ ቅርጽ፣ በኣሁን ዘመን ጎልቶ እንደሚታመነው-- ነገር ግን እውነተኛ ማስረጃ ሊቀርብበት እነዳልቻለው-- የሃሰቱ እውቀት፣ እንደኣሎሎ ክብ እና "በራሷ" ዛቢያ የምትሽከረከር ሳትኾን፣ በኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ት/ትና በኣማንያን እናት አባቶቻችን እንደምንሰማው፣ "ሰማይን [ጠፈርን] ያለባላ፣ ምድርን ያለካስማ ያቆመ ፈጣሪ ኣምላክ" በድንቅ ችሎታው ምድርን የማትንቀሳቀስ በስፋቷ እንደ ምጣድ/ሰፌድ ክብ፣ እና ዝርግ አድርጎ የፈጠራት መኾኑን ማመኔ ነው። [እምነቴን ያስረዳልኛል ብዬ ከተቀበልኳቸው መጽሔተ ሥዕሎት ውስጥ፣ ለማብራሪያ ያህል እነዚህ፣ ከጠቀሙ ብትመለተቱልኝ?** Flat Earth Answers - Proofs and Truths (Full Documentary) እና https://www.youtube.com/watch?v=wlJo2Pp46hw&list=PLoeo3DXEtoNzuZ9jpb_-pj4QPeZ_votuN ]



Flat Earth Answers - Proofs and Truths (Full Documentary...
View on **www.youtube.com** Preview by Yahoo

ስለዚህም ነው፣ ሥዕላዊ መጽሔቱን ስመለከት፣ ከእምነቴ ውጭ ኾኖ በማግኘቴ፣ እንዲሁም፣ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ በዚህ ረገድ ያላትን የእውነትና የመንፈስ ት/ት ለመስፋት በመሻት ይህን "አስተያየትና የሃሳብ ጥቆማ" ስል፡ ርእስ ሰጥቼ መልክት ልጽፍ የቻልኩት።

የእውነት መንፈስ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፣ የሚሰጠኝን ማረጋገጫ ወይም እውነት፣ ለመቀበል እየናፈቅሁ፡ በዚሁ ልሰናበት። ቸር እንሰንብት።

ምስጋናና ውዳሴ፣ ለቅድስት ሥላሴ፣ ድንግል ማርያም ይኹንልን!!! አሜን!

በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያ፣ አክሊለ ጊዮርጊስ።

## ለኪዳናዊ አክሊለ-ጊዮርጊስ የተሰጠ መልስ፡-

### ዮም ፍሥሓ ኮነ!
### በእንተ መዋዕለ ዓቢይ ጾም፡ ዘኢየሱስ መሲሕ!

ይድረስ፡- ለተወደድኸው ኪዳናዊ አክሊለ-ጊዮርጊስ፡-

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትህ ባስገኘልህ፡ የእግዚአብሔር አብወእም ቸርነትና ምሕረት፥ ጸጋና በረከት፡ እየለማና እያደገ፥ እየጐለበተና እየጸና ከኼደው፡ የኪዳናውያንና የኪዳናውያት ቤተሰብህ ጋር፡ በመልካሙ ሕይወት፡ በሓሤት እየኖርህ የምትገኝ በመኾንህ፡ እኛም፡ እዚህ ደስ ብሎን፡ ይህን ያደረጉ፡ የዘላለም አባታችንን እና እናታችንን ከማመስገን አላቋረጥንም።

*"ስለዚህም ነው፣ ...የኪዳናዊ ጋሽዬ ኤርምያስ ከበደን ቃለ መጠይቅ ሥዕላዊ መጽሔት፡ ገና ከመነሻው ላይ ...ስመለከት፣ ከእምነቴ ውጭ ኾኖ በማግኘቴ፣ እንዲሁም፣ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ በዚህ ረገድ ያላትን የእውነትና የመንፈስ ት/ት ለመስማት በመሻት ይህን 'አስተያየትና የሃሳብ ጥቆማ' ስል፡ ርእስ ሰጥቼ መልክት ልጽፍ የቻልኩት።*
*የእውነት መንፈስ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፣ የሚሰጠኝን ማረጋገጫ ወይም እውነት፣ ለመቀበል እየናፈቅሁ፡ በዚሁ ልሰናበት። ቸር እንሰንብት።"* በሚል የመዝጊያ ቃል፡ የመሬትን ጠፍጣፋነትና ክብነት የመላምት አስተሳሰቦችን በሚመለከት፡ መጠይቃዊ አስተያየትህን የያዘ፥ ለኪዳናውያንና ለኪዳናውያት ያሠራጨኸው እ-ጦማርህ፡ ለእኔም ደርሶኝ ተመለከትሁት፤ እግዜር ይስጥልኝ!

በአንድ በኩል፡ በቅዱሱ ኪዳን የተዋሕዶ ሃይማኖታችን ምክንያት፡ እኛ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት፡ "የእግዚአብሔር ልጆች፥ የኢትዮጵያም ልጆች!" ኾነንና ተብለን፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነት፡ ፍጹም እግዚአብሔራዊ፥ ማለትም፡ ፍጹም ተፈጥሮአዊ በኾነው፡ በመልካሙ ሕይወትና እውነት፥ ዕውቀትና ሥርዓት፡ ከሰብአዊው ኪዳነ ልቦና፡ ወደኪዳነ ኦሪቱ ተሻግሮ፡ ለኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ህልውና በበቃው፡ በቅድስቲቱ የትንሣኤና በዘለዓለማዊቷ የሰንበት ገነታዊ ዓለም፡ በምድር ላይ፡ እስካኹን፡ ለ፯ሺ፭፻፲፰ ዓመታት፥ አኹንም እየኖርን፥ ይኸው መለኮታዊው ሕያው ህልውናችንም፡ ወደፊት፡ በዚሁ መልኩና ይዘቱ እየቀጠለ እንገኛለን።

በሌላው ወገን ደግሞ፡ የነፍሳቸውንና የሥጋቸውን አካላትና ባሕርያት፡ በምሥጢረ ተዋሕዶ፡ አንድ አድርጎ፡ ለዚሁ፡ ለእግዚአብሔራዊው መልካም ሕይወት የሚያበቃውን፥ በየራሳቸው ተፈጥሮ ውስጥ፡ ዐብሮአቸው ያለውን፡ መንፈሳዊዉን አካላቸውንና ባሕርያቸውን፡ በገዛ ምርጫቸው፡ "አንፈልግህም! አንጠቀምብህም!" ብለውት፡ በሥጋዊ ነፍስነት ብቻ፡ በዚሁ ምድራዊ ዓለም የሚኖሩት፡ "የሰው ልጆች" የኾኑት፥ እንዲህም ተብለው የሚጠሩት፡ የክፉው ወገኖች ኹሉ፡ ይኸው፡ በዚህ በመረጡት የጥፋት መልክና ይዘት፡ አኹንም፡ ለ፯ሺ፭፻፲፰ ዓመታት፥ እየተሠቃዩና እየተጋደሉ ሲሞቱ ይታያል።

ይኹን እንጂ፡ እነዚሁ፡ የክፉው ወገኖች፡ ከክፉውና ከሓሰቱ፥ ከጥፋቱና ከሞቱ በስተቀር፡ **መልካም የኾነውን እግዚአብሔራዊዉን የሕይወትና የእውነት፥ የዕውቀትና የሥልጣኔ ሥርዓት፡ ጥንትም፥ በመካከሉም፥ ዛሬም፡ ፍንጩን፡ በሙሉ ያገኙት፡ "የእግዚአብሔር ልጆች!" ከኾኑት፡ ከእኒሁ፡ የኢትዮጵያ ልጆች መኾኑ፡ ምንጊዜም** እንዳይዘነጋ ያስፈልጋል።

ይህ አባባል፡ "እነዚሁ የሰው ልጆች፡ ፍንጩ፡ በሙሉ፡ የኢትዮጵያ ልጆች ኾኖ፡ ዛሬ፡ በሥነ-ዕውቀት ምርምራቸውና ጥናታቸው አማካይነት፡ የእግዚአብሔር ከኾነችው፡ ከሥነ-ፍጥረት ምሥጢር ያገኙትን ጠቃሚ ውጤት፡ እውን አድርገው፡ በተግባር ላይ ባዋሉበት ትንግርት ውስጥ፡ ይህንኑ እውነታ፡ በግዝፈት አረጋግጠውት ይታያል!" በሚል አጭር ቃል ተብራርቶ ሊገለጽ ይቻላል።

አዎን! ይህ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ወደጠፈርና በውስጡ ወዳሉት የከዋክብት አካላት፡ እየመጠቁ የሚጓዙባቸውን በራሪ መንኰራኵሮች ለመሥራት ያስቻላቸውን ጥበብ፡ እንዲህ ከማራቀቃቸው በፊት፡ ገና በመጀመሪያው፡ በሥልጣኔ አቡጊዳቸው ጊዜ፡ ከዚሁ ግባቸው ለመድረስ፡ ወጥነው ሲነሡ፡ በምድር ላይ፡ በየብስ የሚሽከረከሩባቸውን ሠረገላዎቻቸውን፥ በባሕር ላይ፡ በውኃ የሚቀዝፉባቸውን መርከቦች፥ በሰማይ ላይ፡ በአየር የሚበሩባቸውን ጥያራዎች፡ ዐቅደው ያበጁበትን፡ የዕውቀትና የጥበብ ክሂሎት ያገኙት፡ ከኢትዮጵያ ልጆች መኾኑን፡ ይኸው እውነታ ያመላክታል። ለዚህም፡ የታወቁትን የአኵስምን ሓውልትና የላሊበላን የአምልኮተ እግዚአብሔር ሕንፃዎች፡ በምስክርነት መጥቀሱ ይበቃል።

ከዚህ የተነሣ፡ በግዙፉ ሥጋዊ ዓይን፡ ክብ ኾነውና እንደኳስ ተድበልብለው እንደሚታዩት፥ በተናጠልና በጋራ፡ በእየራሳቸው የሚያደርጉትን፡ የመሽከርከርና የዙረት [ዑደት] እንቅስቃሴያቸውንም፡ እንደሚያካኼዱት፡ ፀሓይንና ጨረቃን፥ ከዋክብትንና የቀሩትን የጠፈር ቋሚ አካላትን እንደመሰሉት፥ እንደሌሎቹ የሰማይ ሠራዊት ኹሉ፡ <u>መሬትም፥</u> ወይም፡ <u>ምድርም፡</u> በህላዌዋና በህልውናዋ፡ እንዲህ፡ እንደመሰሎቿ የፍጥረት አባላት እንዷ፡ ከእነርሱ ተለይታ የማትታይ የመኾኗን፡ ምሥጢራዊና ተፈጥሮአዊ ዕውቀት፡ እነዚሁ "የሰው ልጆች" የተባሉት፡ የክፉው ወገኖች ያገኙት፡ ከኢትዮጵያ ልጆች ካልኾነ በቀር፡ ታዲያ! ከማን ያገኙታል?

ፍጹም እግዚአብሔራዊ፡ ማለትም፡ ፍጹም ተፈጥሮአዊ በኾነው፡ በመልካሙ ሕይወትና እውነት፥ ዕውቀትና ሥርዓት፡ ይህ ምሥጢር፡ ገና ከመጀመሪያው የተከሠተላቸው የኢትዮጵያ ልጆች፡ "ባሕረ-ሓሳብ" በሚባለው፡ ሥነ ከዋክብትንና ሥነ ቀመርን በሚመለከት፡ ለእኛ፡ ለዛሬዎቹ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን ባቆዩን፡ ሥጋዊ ብቻ ሳይኾን፡ መንፈሳዊ ዕውቀታቸው፡ "ዐውደ-ዕለት"፥ "ዐውደ-ወርኅ"፥ "ዐውደ-ዓመት"፥ "ዐውደ-አበቅቴ"፥ "ዐውደ-ፀሓይ"፥ "ዐውደ-ማኅተም"፥ "ዐውደ-ቀመር" በሚለው የዘመን አቈጣጠራቸው ስልት ውስጥ፡ የመሬትንና የተጓዳኞቿን የአካል ክብነትና የዙረት ህልውናቸውን እውነታ አረጋግጠውልናል።

በእነዚሁ ዐውዳት ምክንያትም፡ በየተወሰኑት የአዝማናት ጊዜያት፡ እነዚሁ፡ የሰማይና የጠፈር አካላት፡ በየዑደታቸው ምሕዋራት [የዙረት መስመራቸው] ላይ፡ የተራክቦ [ግንኙነት፥ ፈረንጆቹም፡ eclipse የሚሉት] ትንግርት የሚደርሰው፡ ከዚሁ እውነታ የተነሣ መኾኑ ሊታወቅ ይገባል።

እንዲሁም፡ "ዙረት" የሚል ትርጉም ያለውና የግእዙን ቃል "ዐውድ"ን ያስገኘው፡ "ዐዊድ"፥ ወይም፡ "ዐዊዶት" የሚለው ዘር፡ "**ለራሱ መዞር፥ መሽከርከር፥ መገላበጥ። ማወድ፥ በዙሪያ መኼድ፥ መመላለስ፥ ማጠር፥ መክበብ፥ ዙሮ መግጠም።**" ማለት በመኾኑ፡ በዚህ ረገድ፡ ስለዚሁ እውነታ፡ ከላይ የተሰጠውን ሓተታ፡ በአጽንዖት ያጠናክረዋል። (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ መጽሓፈ ሰዋስው ወግስ፤ ወመዝገበ ቃላት ሓዲስ፤ ገጽ ፮፻፹፯።)

በዚህ ትርጉም መሠረት፡ ማንም ሰብአዊ ፍጡር፡ በእግሩም ኾነ፡የአኹኑ የዕውቀትና የሥልጣኔ ዘመን፡ እየከየነና እየከወነ በሚያመርታቸው፡ የየብስ፥ የባሕርና የአየር የመጓጓዣ ሠረገላዎች፡ ተሣፍሮም ኾነ እየነዳ፡ ከአንድ ቦታ ተነሥቶ፡ ወደምሥራቅ ኾነ ወደምዕራብ፥ ወደሰሜን ኾነ ወደደቡብ አግጣጫ፡ ቀጥ ብሎ ቢጓዝ፡ ተመልሶ፡ እዚያው እተነሣበት ቦታ እንደሚደርስ እሙንና እውን ኾኖ፡ ይኸው፡ በገቢር እየተፈጸመ ስለሚታይ፡ ይህ እውነታ፡ ስለመሬት ክብነትና ድቡልቡልነት እርግጠኝነት፡ የሚያበረክተውን ተጨባጭ ማስረጃነት ማስተባበል፡ ከቶ የሚቻል አይኾንም።

*"ሰማይን [ጠፈርን] ያለባላ፣ ምድርን ያለካስማ ያቆመ ፈጣሪ አምላክ"* የሚለው፡ የኢትዮጵያ ልጆች ይትበሃል፡ ከዚሁ፡ ከቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ዕውቀትና እውነታ ጋር የሠመረ፡ ማለትም፡ የተስማማና ዐብሮ የሚኼድ መኾኑን በቀላሉ መመልከት ይቻላል።

*"ፈጣሪ አምላክ፡ በድንቅ ችሎታው ምድርን የማትንቀሳቀስ በስፋቷ እንደምጣድ/ሰፌድ ክብ፣ እና ዝርግ አድርጎ ፈጠራት!"* የሚለውን፥ የእውነታው ተቃራኒ የኾነውን ዘይቤ ግን፡ እንደብዙዎቹ ሌሎች ስሕተቶችና ሓሰቶች ኹሉ፡ ያመጡብን፡ በቅድሚያ፡ የዛሬ ሦስት ሽህ ዓመታት፡ ኦሪታውያኑ አይሁድ፥ ቀጥሎም፡ ያንኑ በማጽናት፡ የዛሬ አንድ ሺ ስድስት መቶ ዓመታት፡ ኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች መኾናቸው፡ እዚህ ላይ ሊጤን ይገባዋል።

*"ይህንኑ እምነቴን ያስረዳልኛል ብዬ ከተቀበልኳቸው መጽሔተ ሥዕሎች ውስጥ፣ ለማብራሪያ ያህል እነዚህ፣ ከጠቀሙ ብትመለከቱልኝ?"* በማለት፡ ከእ-ጦማርህ ውስጥ አክለህ ያቀረብኸውና እኔም የተመለከትሁት መጽሔተ-ሥዕልም ቢኾን፡ የእነዚሁ የኦሪታውያኑ አይሁድ እና የኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች ተባባሪ የኾኑ፡ የፀረ-ማርያምና የፀረ-ኢትዮጵያ ሃይማኖታውያን ድርጅቶች፡ በዘመናዊው ኪነታዊ ጥበብ ያቀነባበሩት፡ የአሳሳቹና የምትሓታዊው ፍልስፍናቸው መራራ ፍሬ ሊኾን ስለሚችል፡ ይህንኑ ቅንብር፡ በእውነተኛው መንፈሳዊ አምልኳችን እሳታዊ ኃይል፡ በብርቱ ጥንቃቄ ልንመረምረውና በእግዚአብሔርዋ እውነት ልናጣራው የሚገባን ጉዳይ ነው።

ኪዳናዊ ወንድሜ ሆይ! መሬት፥ ወይም፡ ምድር፡ *"የማትንቀሳቀስ፥ በስፋቷ እንደምጣድ/ሰፌድ ክብ፣ እና ዝርግ"* ትኹን፥ ወይም፡ እኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች እንደምናምነውና *"በገሃድ እንደሚታየው፡ በኅዋ ውስጥ፡ ክብና ድቡልቡል ኾና፡ በራስዋ የምትሽከረከርና ምሕዋርዋን ተከትላ የምትዞር"* ትኹን፡ በፈጣሪ የተሠራውን፡ እውነታውንና ቋሚ የኾነውን፡ የተፈጥሮ ህላዌዋንና የህልውና ሥርዓቷን፡ የማንኛውም፡ የሥጋዊ፡ ኾነ የመንፈሳዊ ፍጡር ዕውቀትና ጥበብ፡ በምንም መልኩና ይዘቱ ሊለውጠው ፈጽሞ እንደማይችል፡ በኹላችንም ዘንድ የታወቀ ነው።

ይልቁንም፡ በዚህ ረገድ የሚነሣው፡ ማንኛውም ዓይነት አስተሳሰብና መላ-ምት፡ የእኛን የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን፡ በምንም መልኩና ይዘቱ የሚነካው ስላልኾነ፡ ይህ ነገር፡ ከዚህ ባለፈ ሊያነጋግረን የሚያስፈልግ አይኾንም። እኔም፡ አኹን፡ ይህን መልስ የጻፍሁልህ፡ ነገሩን፡ በአንተ በኩል ስላነሣኸው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኩል ያለውን አማናዊ ዕውቀት፡ እንድትገነዘበው ለማድረግ ያህል እንጂ፡ ይህን በመሰለ፡ በአንድ አከራካሪ ነጥብ ላይ፡ የውይይት፥ ወይም፡ የክርክር መድረክን ለመክፈት አለመኾኑን ልገልጽልህ እውድዳለሁ።

በያለንበት፡ የተባረከ "ተዝካረ-መዋዕለ-ዓቢይ ጾም ዘኢየሱስ መሲሕ" እንደሚኾንልን እናምናለን።

በቅዱሱ ኪዳን፡ ወንድምህና የአገልግሎት ባልደረባህ፡-

ኪዳናዊ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ [ንቡረ-እድ]